# <u>“ውሸትና ስንቅ እያደረ ይቀላል”</u>!!!

ከባህልቢ ዘማርያም

ውድ አንባቢ!

መጀመርያ፣ ይህ ፀሐፊ ባህልቢ ዘማርያም የብእር ስሙ እንጂ ሐቀኛ ስሙ አለመሆኑን ለመግለጽ ይወዳል።የድረ-ገጽ ጎብኝዎች አይታችሁት እንደሚሆን በተለይ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትና ዳር ድንበራችንን ለሻዓቢያ የለገሰው በአቶ መለስና በአቶ ኢሳያስ ፈቃድ ተግባራዊ ሊደረግ በማኮብኮብ ላይ የሚገኘው የሄግ ብይን ወቅት በዚህ የብእር ስም መጠነኛ ጽሑፎችን በደቂ አሉላ ኋላም በኢትዮሚዲያና ሌላኦች ድረ-ገጾች ላይ ሲያወጣ ቆይቷል። በመሆኑም አነሰም በዛ፣ ሲከታተሉት ለነበሩ አንባቢያን አዲስ ላለመሆን ይዞት በቆየው የብእር ስም ለመቀጠል መርጧል።

በሁለተኛ ደረጃ፣ ይህንን ፅሑፍ አንባቢ ጊዜ አግኝቶ እንዲያነበው በክፍል በክፍል በተከታታይ ይቀርባል። በተጨማሪም፣ ከሐጎስ ዮሐንስ ጽሑፍ ውስጥ ይህ ፀሐፊ ለትችት የመረጣቸውን ወደ አማርኛ ተርጕሟቸዋል። በመሆኑም፣ ምንም እንኳ ትርጉሙን በተቻለ ቃል በቃል ለመተርጐም ቢሞከርም የትርጉም መፋለስ ቢኖርበት ሐላፊነቱን ይወስዳል። ለትርጉሙ አቶ ሐጎስ ዮሐንስ ሐላፊነት የለባቸውም። ባልሆነ ተተረጐመብኝ ካሉም እርማቱን ሲልኩ ለማስተካከል ዝግጁነቱን ይገልጻል።

በሶስተኛ ደረጃ የአቶ ሐጎስ ዮሐንስ ፅሑፍ ከወጣ አንድ ዓመት አልፎታል፤ “ውሸትና ስንቅ እያደረ ይቀላል” እንደሚባለው፣የፃፉትም መረጃ ያልቀረበበት ተራ ቅጥፈት መሆኑም ታይቷል። ሰለሆነም፣ በርእሱ እንደሰፈረው ቀሏልና መተቸት ለምን አስፈለገ የሚሉ ወገኖች መኖራቸው አይቀርም። ሆኖም ይህ ፀሐፊ ጉዳዩ ዘፋኙ እንዳለው “ጉድ አንድ ሰሞን ነው” ተብሎ ሊታለፍ የሚገባው አለመሆኑን አምኖበታል። ከዚህም አልፎ የፈጠራ ወሬን (አንድ ወንድም በስልክ ስብሰባ ላይ በሳሆ “ሆባይ” የሚል ስያሜ የሰጠውን) በመናቅ ለማለፍ እንኳ ቢሞከርም፣ ሰውየው አሉባልታ አወራሁ ብለው በማፈር ፈንታ ዛሬም በስም ማጥፋት ዘመቻው ላይ ለመቀጠል መርጧል። ስለሆነም ቆማጣን ቆማጣ ማለት ተገቢ ይሆናል። ይሁን እንጂ አቶ ግርማይ ተ/ጊዮርጊስና አቶ ኃይለስላሴ ዮሐንስ ያን የመሰለ ትችት ካቀረቡበት በኋላ ለመተቸት መሞከር አስቸጋሪ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቷል። ሆኖም አገርቤት ነዋሪ የሆኑ ወገኖቻችን ሃቁን ለማወቅ በተለያዩ ሁኔታዎች በመገደባቸው አሉባልታውን ከተጨባጭ እውነት ጋር ለማመዛዘን እድል አላገኙም። ስለሆነም፣ በየትም የሚኖር ህዝባችን አሉባልታውን ከእውነቱ ለመለየት እንዲችል ይረዳ ዘንድ ይህንን የሐጎስ ዮሐንስ አሉባልታን በሚመለከት ትንተናውን በአማርኛ ቋንቋ ያቀርቧል።

በተጨማሪም፣ ዛሬ ሐጎስ ዮሐንስ ራሳቸው በፅሑፋቸው ውስጥ እንዳመኑት ከተራ <u>አሉባልታና ያልተረጋገጠ ውንጀላ</u> ተነስተው የሰዎችን መልካም ስም ሥነ-ምግባር ለማጉደፍ ሲነሳሱ ማስረጃውን ያቅርቡ ብሎ መጠየቅ በሞራልም በሕግም አገባብነት አለው። በሳሆ በቋንቋችን አንድ ከጥንት የወረስነው ግሩም አባባል አለ። ይኸውም “ኮክ ሀየከ ኮህ ካለ” በአማርኛ ሲተረጐም አባባሉን በትክክል የሚገልጸው ባይሆንም “ያሸከምከኝን ወንጀል በማስረጃ አስደግፈህ አቅርበው አለበለዛ ግን ከትከሻዬ አንሳልኝ” እንደማለት ነው። ሐጎስ ዮሐንስም እንዱን መምረጥ ይጠበቅባቸዋል። ይኸው ከዓመት በላይ ቢጠበቁም እስከዛሬ እንኳን ማስረጃ፣ መረጃም ማቅረብ አልቻሉም። ይህም የሆነው በሌላ ምክንያት ሳይሆን ለውሸት ማስረጃ ማቅረብ ስለማይቻል ብቻ ነው። በመሆኑም፣ ከእንግዲህ ድርቅና ካልሆነ በስተቀር ያሳሳቱትን ህብረተ-ሰብ ይቅርታ ከመጠየቅ ውጭ ሌላ አማራጭ

አይኖራቸውም። ይህንን ዓይነት ቅጥፈት በጋራ ሁነን በጊዜ ካላስወገድነውና ካላስቆምነው ሰላም የሰፈነበት ሕብረተ-ሰብ ለመፍጠር ፈጽሞ እንደማይቻል ከወዲሁ መታወቅ አለበት። ለዚህም ነው፤ ይህ ፀሐፊ የሐጎስ ዮሐንስን ፅሑፍ ለመተቸት የመረጠው። አሉባልታና ውሸት ለማፍረስ እንጂ ለመገንባት አይሆኑም። የዚህ ዓይነት ባሕሪ የተላበሱ ሰዎችን የመግራት ሸክም ለተወሰኑ ሰዎች የሚተው ግዳጅ አይደለም። ሁሉም በጋራ ሊያከሽፈውና ሊመክተው የሚገባ የጋራ ጉዳይ ነው። ውሸታም ካልተጋለጠ ዛሬ አንዱ ላይ ነገ በሌላው ላይ እያለ የፈጠራ ወሬ እየነዛ ህብረተሰብን እየመረዘ ይቀጥላልና። ሐጎስ ዮሐንስ ዛሬ የተወሰኑ ካድሬዎችን ከጎን በማሰለፍ የማትረባ ጉርሻ ማግኘት ይቻል ይሆናል። ቢያንስ ጎበዝ በርታ ጥሩ ሠርተሃል የሚል መልእክት ያላት የትከሻ ምት፤ ገፋ ቢል ደግሞ ከአንድ አንስተኛ ባለሥልጣን ጋር ፎቶ የመነሳት ዕድል ትፈጥር ይሆናል። ከዛ ያለፈ እርባና ያለው ነፃ ሰው ሆኖ ማግኘት የማይቻለውን ጥቅም ማግኘት ግን አይታሰብም። ከተገኘም የታጨበትን አገልግሎት ስጨርሱ የሚያከትም ይሆናል። ከዛ ያለፈ ፋይዳ አይገኝም።

በአራተኛ ደረጃ፤ ይህ ፀሐፊ ሐጎስ ዮሐንስና መሰል ወዶ ገብ ካድሬዎች፤ እንደሚያደርጉት ከአሉባልታ እንደማይነሳ ለአንባቢ ለማረጋገጥ ይወዳል። የሚዋጋውና ማክተም አለበት ብሎም የሚያምነው አሉባልታና የፈጠራ ወሬን ነው። የውስጥ ሰላም ያለው ህብረተ-ሰብ ለመፍጠር የምንታገል ኃይሎች ከሁሉም አስቀድመን መታገል ያለብን ውሸትንና አሉባልታን እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል። ሕብረተ-ሰብ በሰላም እንዲኖር፤ ተሳስቦና ተፋቅሮ ለጋራ ዓላማ አብሮ እንዲቆም የውስጥ ሰላም ወሳኝ ተራ አለው። ፈረንጆች አንድ ጥሩ አባባል አላቸው (united we stand, divided we fall) "ከተባበርን እንቋቋመዋለን፤ ከተከፋፈልን እንወድቃለን" የሚል። ይህ ፀሐፊም በዚህ ፍቱን አባባል እጅጉን ይማረካል። አቅሙ በፈቀደም በተግባር ሊያውለው ይሞክራል። በመሆኑም የሐጎስ ዮሐንስና አጃቢዎቻቸው ወዶ-ገብ ካድሬዎች አሉባልታና የፈጠራ ወሬዎችን እውነተኛ ጭብጦችና በአመክንዮ የተደገፉ ክርክሮችን በማቅረብ አሉባልታን ከሚዋጉ ወገኖቹ ጎን ቆሞ ለመመከት ቃል ይገባል። እነዚህ ወዶ-ገብ ካድሬዎች እውነትን ማውራት እስኪጀምሩም እንደሚቀጥል ያረጋግጣል። ሰው የማይሰማማበት አመለካከት ሲኖር የመከራከርያ ጭብጥ አቅርቦ በመክንዮ አስደግፎ ሲከራከር ማየት የመንፈስ ቅናት ያሳድራል ብቻ ሳይሆን፤ አዳዲስ ለሚፈልቁ ሐሳቦች ጥልቀት ይረዳል። ሰዎች አማራጮችን እንዲያቀርቡ ዕድል በመፍጠር ውሸትና አሉባልታን ያስወግዳል። ውሸት ምን ቢደጋገም ጠብታ እውነት ሊወጣበት አይችልም። አሉባልታን በመንዛት የሚፈራ በራሱ የሚተማመን ሰው ደግሞ አይኖርም። በመሆኑም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሐጎስ ዮሐንስን አሉባልታዎች በአመክንዮ አስደግፎ ለመተንተን ይሞክራል። እውነትን የሚሹዋት ወገኖች በነሐጎስ ዮሐንስ አሉባልታ መፈታት አይኖርባቸውም። ሐጎስ ዮሐንስና መሰል ወዶ-ገብ ካድሬዎች ጭብጥ ይዘው እንዲቀርቡ እንደቆዳ ተወጥረው መያዝ ይኖርባቸዋል። በዚህና በዚህ ብቻ ነው ለወደፊትም ቢሆን አሉባልተኞች እንዳይፈጠሩ መከላከል የሚቻለው።

እንግዲህ ወደ ቁምነገሩ እንግባ! የዛሬ ዓመት በዚህ ወቅት ሐጎስ ዮሐንስ እ.ኤ.አ ታሕሣሥ 31 ቀን 2009 በፈረንጆች አዲስ ዓመት ዋዜማ ዕለት "ከዕድሜ በታች የሆኑ ሕፃናትን ለጦርነት መመልመል ሰብአዊነትን መፃረርና ዓለም ዓቀፍ ሕግን መጣስ ነው" ("RECRUITMENT OF UNDERAGE CHILDREN IN WAR IS AGAINST HUMANITY AND VIOLATION OF INTERNATIONAL LAW.") በሚል ርእስ አንድ ፅሑፍ አውጥተው ነበር። ይህ ጽሑፍ በመጀመርያ የህወሓት ልሳን በሆነውና ዓይጋፎሩም በሚል መጠርያ በሚታወቀው ድረ-ገጽ ከቀናት በኋላም በwww.irrob.org ላይ ተለጥፎ አይተነዋል። ይህ የተጠቀሰው ፀሑፍ በwww.irrob.org ድረ-ገጽ ላይ እንደወጣ የማኅበረ-ሰቡ አባላት ለውይይት በተዘጋጀው የድረ-ገጹ የመወያያ መድረክ

መድረኩ (forum) እስከተዘጋበት ዕለት ድረስ የሐጎስ ዮሐንስን መጣጥፍ ደጋፊና ተቃዋሚ ጎራ አስለይቶ ሲያወዛግብ መሰንበቱም ይታወሳል። በዚህ የውይይት መድረክ ላይ ሲደረጉ በነበሩ ውይይቶች ላይ እጅጉን አንቱ የሚያሰኝ፤ ለራስ ሂልና የሞራል የበላይነት የሚያጎናጽፍ፤ የአንባቢን አመለካከትም ለመግራት የሚያስችል አስተያየት የሰነዘሩ አንቱ የሚባሉና ለመባልም የሚገባቸው የተወሰኑ ብርቅዬ ወገኖች እንዳሉን ለመታዘብ አስችሎናል። ለነዚህ ለማንም ሳይሆን ለሂሊናቸው ለቆሙ ወገኖቻችን ይህ ፀሐፊ ባርኔጣውን ሊያነሳላቸው ይወዳል። በቁጥር አንስተኛ ቢሆኑም ለሕብረተ-ሰባችን ደህንነት ምርጥ እርሾዎች ናቸውና ወዳጅም ጠላትም ሊያከብራቸው ይገባል። ለሂሊናቸው እንጂ ለማንም ዋሾ እንደማይንበረከኩም አስመስክሯል። በሌላ በኩል ደግሞ የተወሰኑ አንቱ ለመባል የበቁበት የዕድሜ ክልል ውስጥ የገቡና መጥፎን መጥፎ ማለት የሚጠበቅባቸው ሰዎች ራሳቸውን ያዋረዱበት ሁኔታንም ለመታዘብ ችለናል። ይህ ፀሐፊም በመድረኩ ላይ አንድ አጭር መልእክት በማስቀመጥ፤ መጀመርያ ህዝብ በቴሌ-ኮንፈረንስ ተገናኝቶ መረጃ እንዲቀርብ ሐጎስ ዮሐንስን ይጠይቅ የሚል ሓሳብ በመደገፍ መጨረሻ ላይ ግን በፅሑፉ ላይ የራሱን አስተያየት እንደሚያቀርብ አስፍሮ ነበር። ሆኖም መስተናገድ የሚፈለገው ከተስተናገደ በኋላ የድረ-ገጹ ባለቤቶች መድረኩን በመዝጋታቸውና ይህንን ፅሑፍ አስመልክቶ ምንም ዓይነት ፀሑፍ ለማስተናገድ ዝግጁ እንዳልሆነ በመግለጹ እስከዛሬ ድረስ በሐጎስ ዮሐንስ ፅሑፍ ላይ አስተያየት የመስጠት ዕድል ሳያገኝ ቆይቷል። በመሆኑም፤ ይኸው ዛሬ በሐጎስ ዮሐንስ ፅሑፍ ላይ እይታውን ለማስፈር በዚሁ የሚጀምር ቢሆንም ባጠቃላይ በተጠቀሰው ፅሑፍ ምክንያት የታዩ ክስተቶችን በመጠኑ ማቅረብ አጠቃላይ የፅሑፉን የአሁንና በቀጣይ የህብረተ-ሰባችን አንድነት ላይ የሚያጠላው እድምታ ምን ሊመስል እንደሚችል ለመገመት ይረዳል።

ሐጎስ ዮሐንስ! የፃፉት ጽሑፍ በአመክንዮ የተደገፈ አይደለም። ይኸው! ጽሑፍዎን ካቀረቡ ከአንድ ዓመት ከአንድ ወር በላይ ያለፈ ቢሆንም እስከዛሬ ጠብ የሚል ማስረጃ ሲቀርብና ክስ ሲመሠረት አልታየም። ይህ ደግሞ በሚገባ ተጠንቶ በስልት የተቀናጀ እንጂ ባጋጣሚ የተደረገ ተራ ስሕተት እንዳልሆነ ያሳያል። ይህ ይበልጥ ግልጽ የሚሆነው ያ ፅሑፍ የወጣ ወቅት የነበረው የካድሬዎች መሰባሰብና አደረጃጀትን በቅጡ መርምሮ ሲታይ ነው። በዛ ሰሞን ሐጎስ ዮሐንስና በእሳቸው ዙርያ የተሰባሰቡ ካድሬዎች ይዘውት ይዞሩ የነበሩት የእጅ ስልክ የደርግ አገዛዝ ወቅት የነበሩት የቀበሌ ተላላኪዎች ይዘውት ይዞሩ የነበረ የድምጽ ማጉያ ጋር ማመሳሰል ይቻላል።”ወዮልህ ቀበሌ ስብሰባ ባትገኝ” ይባል እንደነበረ ሁሉ የአሁኖቹ አዲስ የሕወሓት ምልምል ካድሬዎችም “ወዮልህ በፈጠራ ውንጀላ ያላመንክ” በማለት ስልክ ያልደወሉበት የኢሮብ ተወላጅ ቤት ቢኖር በጣም ውስን ነው። ከዚህም አልፎ አንድ የዱለታ ቡድን ተቋቁሞ በውጭ በሚኖር የኢሮብ ማህበረሰብ አባላት ውስጥ ከፍተኛ ወከባ ፈጥሮ የነበረ መሆኑንም የሚታወስ ነው።

የሐጎስ ዮሐንስ ፅሐፍ በሰሜን አሜሪካና ኤውሮጳ ነዋሪ የኢሮብ ተወላጆችን በሕፃናት ምልመላ ፈርጆ ያወጣ ቢሆንም፤ መላው በውጭ አገር ነዋሪ የኢሮብ ብሔረ-ሰብ ተወላጆች ሊሳተፉበት የሚችል የስልክ ስብሰባ ተጠርቶ በጥያቄ ሲዋከቡ ጠላትን መቀነስ በሚል አጕል ታክቲክ “እኔ ለመወንጀል የፈለግሁት ኢ.መ.ተ.ማን (IRAA) ነው በማለት ሸብረክ ማለታቸው የሚታወስ ነው። የሚያሳዝነው ግን ቤቱ ማንም ይሁን ማንም ችግሩ የኢሮብ ህዝብ ነውና ጥፋተኞች መጠየቅ ስላለባቸው ማስረጃውን አምጣ ብሎ ወጥሮ መያዝ በተገባ ነበር። ሆኖም ብዙቻችን ነገሮችን ራቅ አድርገን ለመመልከት ወይም አልፈለግንም፤ አለዛም አልደፈርንም። ቀጥሎ ኢ.መ.ተ.ማ የፈሪ ዱላው ወደሱ አቅጣጫ እያቀና መሆኑን ስለተገነዘበ እ.ኤ.አ ጥር 31 ቀን 2010 አሁንም በውጭ አገር የሚኖር የኢሮብ ተወላጅ ሊሳተፍበት የሚችል ክፍት የተሌፎን ስብሰባ ጠርቶ ራሱን በወጉ ከህዝብ ጋር በማስተዋወቅ በዕለቱ የተነሱትን ጥያቄዎች በሚገባ መልሶ ነበር። ከዚህም አልፎ

በዕለቱ የተሰበሰበው ሰው የሐጎስ ዮሐንስ ፅሑፍን በሚመለከት መርምሮ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንዲያደርግ አምስት ሰው ያለበት አንድ ኮሚቴ ተዋቅሮ ስብሰባው በሰላም ተጠናቅቆ ነበር። የሆነ ሆኖ የዕለቱ ስብሰባ እ.ኤ.አ በካቲት 7 ቀን 2010 ለመገናኘት ስምምነት ላይ ተደርሶ ተቋጭቶ ነበር።

በዚህ ማኸል በሐጎስ ዮሐንስ የአሉባልታ ፅሑፍ ላይ ተመርኵዞ የየግል ቁርሾው መወጣጫ አጋጣሚ ሲያፈላልግ የቆየ በአንድ የካድሬዎች ቡድን የሚመራ አኹራፊ የአድማ ቡድን ተፈጠረ። ይህ አድመኛ የኵርፊያ ቡድን ለየካቲ 7 ቀን 2010 የተቀጠረው ስብሰባ ላይ ራሱን አቀናጅቶ ለመቅረብ የሚያስችለው አጀንዳ ለመቅረጽ እ.ኤ.አ የካቲት 3 ቀን 2010 ዓ.ም ተጠራርቶ የቡድን የድብቅ የስልክ ስብሰባ ማድረጉም ይታወቃል። ኋላ ላይ በተግባር የታየው ክስተት እንደሚያመለክተው  የስብሰባው ዋና ዓላማ ለየካቲት 7 ቀን 2010 የተቀጠረው ስብሰባ ላይ ኢ.መ.ተ.ማ አመለካከቱና ዓላማውን ለህዝብ ይፋ የማድረግ ዕድል እንዳያገኝ ምን ማድረግ እንዳለበትና እንዴት ማኮላሸት እንዳለበት ለመወያየት ነበር። በዚህ መሠረትም እ.ኤ.አ በየካቲት 3 ቀን 2010 ዓ.ም ለብቻ መሰብሰቡን ሳይገልጽ የካቲት እ.ኤ.አ የካቲት 7 ቀን 2010 ለኢ.መ.ተ.ማ የሚቀርቡ ጥያቄዎች አሉ በማለት ጥያቄዎች እንዳሉት መስሎ ለመቅረብ ሞክሯል። ይህን ሲያደርግ ግን ለኢ.መ.ተ.ማ የሚቀርብ ጥያቄ መኖሩን የሚገልጽ የስብሰባ አጀንዳ አልተሰራጨም። ስብሰባውን ሲያዘጋጁ የነበሩ ወገኖችም አጀንዳውን ለማሰራጨት አልፈለጉም ወይም በቸልታ አይተውታል። የኢ.መ.ተ.ማ አባላት የኢሮብ ስብሰባ ይመለከተናል ብለው አስቀድሞ በተቆረጠው ቀነ ቀጠሮ መሠረት በስልክ ህዝባዊ ስብሰባው ላይ ተገኝቷል። አዘጋጆቹ ያስተላለፉት የመወያያ አጀንዳ ስላልነበረ ሁሉም አብዛኛው የሚጠብቀው የዕለቱን አጀንዳ ለመስማት ነበር። የዕለቱ ሊቀ-መንበር ስብሰባውን ከከፈተ በኋላ ከወዶ-ገብ ካድሬዎች አንዱ ዛሬ ለኢ.መ.ተ.ማ የሚቀርቡ ጥያቄዎች አሉን ብሎ ንግግር ይጀምራል። ያኔ መጀመርያ የእለቱ መወያያ አጀንዳ ምን እንደሆነ ለቤቱ ይገለጽ የሚል ሐሳብ በአቶ ኃይለስላሴ ዮሐንስ ይሰነዘራል። ጥያቄው በሌሎችም ይስተጋባል። የእለቱ የስብሰባ መሪ ግን አጀንዳው ምንድነው የሚለው ጥያቄ እንዲስተናገድ አልፈቀዱም። ጥያቄው ገፍቶ ሲመጣ የወዶ-ገብ ካድሬዎች አድመኛ ቡድን የዚህ ዓይነት ጥያቄ መነሳት ሊያጋልጠው እንደሚችል ግምት ውስጥ አስገብቶ ስለቆየ የተለያዩ፤ የድምጽ ሞገዶችን በመስደድ የስልክ ስብሰባውን መረበሽ ጀመረ። ለዚህም ልክ ስብሰባው ተረብሾ መቀጠል የማይቻልበት ደረጃ ላይ መድረሱ እንደተረጋገጠ አድመኛው ቡድን በቀጥታ የራሱ የቡድን የስልክ ስብሰባ በማካሄድ ያረጋገጠው ሀቅ ነው። እዚህ ላይ የወዶ-ገብ ካድሬዎቹ ቡድን አስቀድሞ የተስማማበትና አስቀድሞ ተዘጋጅቶበት ባይቆይ ኖሮ በዛ ቅጽበት የስልክ ስብሰባ ማድረግ እንደማይችል መታወቅ አለበት። ይህ ፀሐፊ የወደ-ገብ ካድሬዎች ስብስብ ያካሄደው ውይይትን በሚመለከት ለጊዜው ዝርዝሩን ከማቅረብ ለመቆጠብ መርጧል። ሆኖም ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎችን ማንሳት ተገቢ ይሆናል። ይህ የወዶ ገብ ካድሬዎች ጥርቅም እውነት ለኢ.መ.ተ.ማ የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ኖረውት ከሆነና በቅን ልቦና የኢ.መ.ተ.ማን ዓላማ ተረድቶ ጥሩና መጥፎ ጎኑን ለመመርመር የሚፈልግ ከሆነ ጥያቄዎች አሉኝና የሚመለከታቹህ የኢ.መ.ተ.ማ አባሎች በዕለቱ ስብሰባ ተገኙ ብሎ መልእክት ለማስተላለፍ ለምን አልፈለገም? አጋጣሚ ሆኖ በተለያዩ ምክንያቶች የኢ.መ.ተ.ማ አባሎች በስልክ ስብሰባው ሳይገኙ ቀርተው ቢሆኑ ኖሮስ? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳትና ማየት ተገቢ ይሆናል። ቡድኑ ይህንን ለማድረግ አለመፈለጉ ሁለት እድምታዎች እንዳሉት በግልጽ ይታያል። አንደኛው እድምታ ያልተጠበቀ ጥያቄ አቅርቤ በማፋጠጥ ለማጥቃት እችላለሁ የሚል አጉልና ርካሽ ተንኮል በመጠንጠን ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በሆነ አጋጣሚ የኢ.መ.ተ.ማ አባላት በስብሰባው ለመገኘት ሳይችሉ ቢቀሩ በስልክ ስብሰባው

በተለመደው የአሉባልታ ፕሮፓጋንዳው፤ ስብሰባው ላይ ተገኝተው ለጥያቄዎቻችን መልስ እንዲሰጡ ጠይቀናቸው ፈርተው ሳይሳተፉ ቀሩ የሚል አሉባልታ በማውራት የህዝብን አመለካከት ለመበረዝ የተሸረበ ተንኰል ነው። ሁለቱም ስልቶች ሲከሽፉበት ስብሰባውን ረብሾ በመውጣት የአሉባልታ ስም የማጥፋት ስልት ላይ ተወያይቷል። ይህንን ተከትሎ አንድ ስሙንም ጭምር ልጠቅሰው የማልፈልገው ሰው tigraionline.com በሚባል የህወሓት ድረ-ገጽ ላይ ተራ ስድብና ውረፋ ያቀፈ አንድ አስቀያሚ ነገር ተለጥፎ ለማየት በቅተናል። የዛ ሰው ወረቀት ከስድብ ውጭ የያዘው ነገር ቢኖር ማስጠንቀቅያና ማስፈራርያ ብቻ ነው። ይህ ፀሐፊ መሳደብ አይችልም ብቻ ሳይሆን እንደ ቁምነገርም ስለማይቆጥረው፤ ያንን ወረቀት በሚመለከት አስተያየት በመስጠት ራሱ ወደዛ ደረጃ ለማውረድ ፈቃደኛ አይደለም። ማስፈራርያውና ማስጠንቀቅያውን በሚመለከት ግን መቼም ተመልሶ እናት ሆድ አይገባ! መመመመመጠበቅ ነዋ የኔ ጌታ!!!

ለዛሬ በዚህ ሁሉ ውይይት ማኸል እ.ኤ.አ ጥር 31 ቀን 2010 ኢ.መ.ተ.ማ በጠራው ህዝባዊ የስልክ ስብሰባ ላይ አንዲት የዋህ እህት ያቀረበችውን ጥያቄ ለማሳቅ ያህል አካፊያቹ ልቋጨው። ሐጎስ ዮሐንስ IRAA የኢሮብ ሕፃናትን ለሻዓቢያ ይመለምላል የሚል አሉባልታ አውጥተው ሲያበቁ፤ መረጃ አምጣ የሚል ጥያቄ ሲቀርብ፤ “ታማይ ዳ ማፋኪና ዱደ ኤታነ” ወደ አማሪኛ ሲተረጐም “ያንን ድንጋይ አትክፈቱ ጉንዳን አለበት” በማለት አሰላችተውን በነበረበት ሰዓት ላይ “IRAA እሮ በያይ ማታነም ማስረጃ ባህቶይ” ሲተረጐም “IRAA ልጆችን ለሻዓቢያ አለመመልመላቹህ ማስረጃ አቅርቡ” ያለችው አዳምጩ የዋህነቷ ቢያሳዝነኝም በዛን ሰዓት ፍርስ ብዬ እንድስቅ ላደረገችው አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባታል። ኧረ ወዲያ ፍርድ መስጠት ካልቀረ እንዲህ ነው እንጂ ወገን!!!!

ነብሳቸውን ይማርና በአንድ ሰንበት ክቡር አባ ኃይለሚካኤል ወልደማርያም ልደታ ማርያም ቤተክርስትያን ውስጥ ሲሰብኩ “አኑ ጉረም ሐቀ ዲራቢሊ ጉረም ዮዋ ትብ አከ” የሚለው ዘፈን እጅጉን ትልቅ ተስፋ ይሰጠኛል ብለው ነብር። ዘፈኑ በወቅቱ ሲዘፈን የነበረ በመሆኑ ባውቀውም የሳቸው አነጋገር ግን ጣዕም ነበረውና አይረሳም፤ ሰለሆነም ይህ ፀሐፊም ያንን በመድገም “አኑ ጉረም ሐቀ ዲራቢሊ ጉረም ዮዋ ቲብ አከ” በማለት በሚቀጥለው እስክንገናን ለዛሬ በዚህ ይሰናበታል!!!!!!! ሉሁሉም መልካም ሳምንት!

ይቀጥላል……………..

የካቲት 5 ቀን 2011 ዓ.ም.ፈ